# አስፋው ፊለቀና እጅጋየሁ ያለው
# በጦርነቱም በድሉም ያልተለያዩ ጀግና ባልና ሚስት

(አዲስ ዘመን ጋዜጣ፡ **ምን ሠርተው ታወቁ?** አዘጋጅ ነቢዩ እያሱ)
ግንቦት 15 ቀን 1980 ዓ.ም.

<<ባልና ሚስት ከአንድ ውሀ ይቀዳል >> ይባላል ፡፡ አቶ አስፋው ፊለቀና ባለቤታቸው ወ/ሮ እጅጋየሁ ያለው በነጻነት ትግሉና በመከራውም ፡ በድሉና በደስታውም ያልተለያዩ ተጋዳይ አርበኞች ናቸው፡፡ አንድ አካል አንድ አምሳል የሆኑ እውነተኛ የእድሜ ልክ ጓደኞች ናቸው፡፡ በፍቅር የተሳሰሩና በሀገር ፍቅር የነደዱ የነጻነት ታጋዮች በመሆን የማያልፍና አርአያነቱ የጎላ የአርበኝነት ታሪክ ሰርተዋል ፡፡ ወ/ሮ እጅጋየሁ ያለው ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩም በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ የፈጸሙት የአርበኝነት ተጋድሉ ለአዲሱ ትውልድ አርአያነት ያለው ነው ፡፡

አቶ አስፋው ፊለቀ በዚያን ሰሞን ወደ ቢሮአችን ብቅ ብለው ስለጥንቱ የተጋድሉ ታሪካቸው ሲያወጉን ዛሬም ያ የቀድሞው ወኔና ቁርጠኝነት ፊታቸው ላይ ይነበባል፡፡ የሀገር ፍቅር ስሜታቸው ጨርሶ አልቀዘቀዘም፡፡ በሀገር ነጻነትና አንድነት ላይ ያላቸው አቋም ቅንጣት ያህል አልተናጋም፡፡ በሕዝባዊ ዓላማ ጸንቶ መኖር እንዲህ ነው፡፡

ወ/ሮ እጅጋየሁን በአካል አግኝተን ልናነጋግራቸው ባንታደልም የአርበኝነት ተጋድሎአቸውን ከታሪካቸው ልንረዳ ችለናል፡፡ ወ /ሮ እጅጋየሁ ፋሽስት ኢጣሊያ አገራችንን በወረረ ጊዜ ከባለቤታቸው ከአቶ አስፋው ፊለቀ ጋር በመዝመት በጎፋ ፡ በአካባ ፡ በከንባታ ፡ በኩሉ ኮንታ ፡ ከጠላት ጋር ከፍተኛ



አቶ አስፋው ፊለቀ ፥

ተጋድሎ አድርገዋል፡፡ የጠላት ጦር በመርዝ ጢስ በመጠቀምና በዘመናዊ ጦር መሣሪያ የአርበኞችን ሠራዊት ለመበተን ቢሞክርም ብዙ ተከራክረውታል፡፡ በዚሁ ተጋድሎ ወ/ሮ እጅጋየሁ የቆሰለውን በማከም

የደከመውን በማበረታታት የሴትነት ድካምና ፍርሀት ሳይሰማቸው ያደረጉት ተጋድሎ በሕይወት ያሉ ጀግኖች አርበኞች የሚያደንቁት ነው:: ኋላም በስደት ኬንያ በመግባትና ተመልሰውም ከቀዳሚው ተዋጊ ጦር ጋር ወደ ኢትዮጵያ በሲዳሞ በኩል በመግባት ከባለቤታቸው ጋር ለነጻነት ድል በቅተዋል::



ወይዘሮ እጅጋየሁ ያለው ፡

አቶ አሰፋው ፈለቀ በ1928 ዓ.ም. ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትወር በራሳቸው ፈቃድ ከዲላ ተነስተው የራስ ደስታ ዳምጠው ጦር ወደለበት ወደ ዋደራ በመጓዝ የጦርነቱ ተካፋይ ሆነዋል:: ከዚያም የጠላት ጦር በማየሉ በሌላ አቅጣጫ ከሌሉች አርበኞች ጋር ተንቀሳቅሰው ጀባስሬ ላይ በጨበጣ ውጊያ ሳይቀር በጀግንነት ተዋግተው ለጠላት ጦር መደከም ድርሻ አበርክተዋል:: ቀጥሎም በአገረማርያም: በዋጭሌ: በገላናና በልዩ ልዩ ሥፍራ በተደረጉት ጦርነቶች ጠላትን አሳረማምድ በማለት ተከላክለዋል::

የኢጣሊያ ጦር በአውሮፕላኖች ቦምብና የመርዝ ጢስ በማርከፍከፍ በወገን ጦር ላይ ከባድ እልቂት አድርሶ ዋዴራንና ጀባስሬን ሰብሮ ወደመሀል አገር በመግባት ወላይታን ይዞ ወደ ገሙ ጨንቻ በማምራት የአርበኞችን ጦር ከቦ ለመያዝ ማሰቡን ስለደረሱበት አቶ አሰፋው የሚገኙበት የአርበኞች ጦር መጋቢት 5 ቀን 1929 ዓ.ም. ወደ ጨንቻ ተጓዘ::

ይህም አካባቢ ምቹ ሆኖ ባለመገኘቱና ሕዝቡ ተወናብዶ ለጠላት ጦር መንገድ መምራት በመጀመሩ የአርበኞች ጦር ወደ ጎፋ ወረደ:: በዚያም ለማጥቃት የመጣውን የጠላት ኃይል ማኬ ላይ ጠብቀው በመግጠም ጓዙን ጥሎ እስኪሸሽ ድረስ ድል አድርገው አባረሩት:: አቶ አሰፋው ፈለቀ በዚህ ውጊያ ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ የጠላትን ጦር የረፈረፉ ሲሆን ከተሰዉ የወገን ጦር አባላት መሣሪያ በማንሳት ለባልደረቦቻቸው አስረከበዋል::

በመጨረሻ በዚህ ዓይነት መቀጠሉ ስለማያዋጣ የአርበኞች ጦር ጓዙን ኬንያ አስቀምጦ በደረቅ ጦር በመቀጠል በደፈጣ እየገባ ጠላትን እንዲያምስ በምክር ስለተወሰነ ሰኔ 23 ቀን 1929 ዓ.ም. በገለብ በረሀና በሩዶልፍ ሐይቅ አድርገው ኬንያ ገቡ:: ከዚያም ከእንግሊዝ ሹማምንት የተላኩ ወታደሮች የአርበኞችን ጦር አባሉች መሣሪያቸውን በመረከብ በስደት እንዲኖሩ ወደተወሰነላቸው ቦታ ወደ ሲኦሉ ወሰዱአቸው:: ከዚያም ወደ ታቤታ ተወስደው በጠቅላላው ለሶስት ዓመት በስደት ኬንያ ቆዩ:: በዚያም ለስደተኞች ልጆች በተከፈተው ትምህርት ቤት ለተመላላሽ ተማሪዎች ምክትል ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል::

በ1932 ዓ.ም. ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተጀመረ :: ጣሊያንና እንግሊዝም በክልሉ በቅኝ በያዟቸው አገሮች ድንበሮች ላይ ቁርቋሶ ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ ኬንያ ከነበሩት ስደተኞች ውስጥ እንግሊዞች አምስት መቶ ሰዎች መርጠው ወደ ጠረፍ ሲወስዱ አቶ አስፋው አንዱ ነበሩ:: በዚህ ሁኔታ ወደ ማጅ ተጉዘው ሸተት ባይ በተሰኘው ቦታ ላይ የጠላትን ጦር ወግተው አባረሩት ነገር ግን የሚበላ ባለመኖሩ ጦሩ ስለተቸገረ ሳርና ቅጠል እየበላ ወደ ወሰኑ ተመለሰ::

በኋላም ጦሩ እንዲያገግም ተደርጎ በቦረና በኩል ለስለላ ጠልቆ እየገቡ መረጃ የሚያቀብሉ ሁለት መቶ ስድሳ ሰዎች ሲሰማሩ አንዱ አቶ አስፋው ነበሩ:: በዚህ ተግባር ላይ እንደቆዩ የእንግሊዝ ጦር ሲመጣላቸውና ጦርነቱ ሲጀመር በአልዲያ: በሆቦቅ: በዱከና: በሐመርና በሌሎችም ልዩ ልዩ ሥፍራዎች በተደረጉት ውጊያዎች የጦር መሪና አስተርጓሚ በመሆን በሀምሳ አለቅነት አገልግለዋል ::

ሚያዝያ 12 ቀን 1933 ዓ.ም. ከእንግሊዙ አለቃቸው ጋር ለስለላ ተንቀሳቅሰው ሳለ የጠላት ጦር ደርሶባቸው በብርቱ ትግል ቀጥሩ የበዛውን ጠላት አሸንፈው ለመመለስ ከመቻላቸውም በላይ አንድ ከባድ መትረየስና ሁለት ቀላል መትረየሶች ከአምስት የጠላት ወታደሮች ጋር ማርከዋል:: ከዚያም ወደፊት በመቀጠል በመንገድ መሽጎ የነበረ የጠላት ጦር ወግተው አስለቅቀዋል:: አቶ አስፋው በዚህ ውጊያም በቦምብ ፍንጣሪ አንድ ዓይናቸው ጠፍቷል:: እንዲህ ዓይነት ጉዳት ደርሶባቸው እየደሙ እያለ ከአጠገባቸው የሞተ ባልደረባቸውን አስከሬን አስነስተው አስቀብረዋል:: በዚህ ተግባራቸውም በእንግሊዝ ጦር አዛዦችና በኬንያ ጋዜጦች ተደንቀዋል:: በዚህም ውጤታቸው የእንግሊዝ መንግሥት የኪንግ ጆርጅ ስድስተኛ የጀብዱ ሜዳይ ተሸልመዋል::

ከነጻነት በኋላ በአስተዳደር ሥራ በተለያዩ ክፍላተ ሀገር ከማገልገላቸውም በላይ የጠቅላይ ግምጃ ቤት ምክትል ገንዘብ ያዥና በኋላም ዋና ገንዘብ ያዥ ሆነው ሠርተዋል:: ከዚያም በ1967 ዓ.ም. በጡረታ ተገልለዋል ::

አቶ አስፋው ፈለቀ በዚህ ሁሉ አገልግሎታቸው በርካታ የሜዳይ ሽልማት ተቀብለዋል:: ከእነዚህም ውስጥ የአንድ ዓመት የአርበኝነት ሜዳይ ባለአንድ ዘንባባ: የስደተኝነት ሜዳይ: የድል ሜዳይ: የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የጀብዱ ሜዳይ: የእንግሊዝ መንግሥት የምሥራቅ አፍሪካ ሜዳይና የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የፈረሰኛ ደረጃ ይገኙባቸዋል::

ህዳር 7 ቀን 1907 ዓ.ም. ከአባታቸው ከአቶ ፈለቀ ወልደተክሌና ከእናታቸው ከወይዘሮ ደስታ አየለ በከፋ ክፍለ ሀገር በኮንታ አመያ የተወለዱት አቶ አስፋው ከባለቤታቸው ወ/ሮ አጅጋየሁ ጋር ልጆቻቸውን በሚገባ አስተምረው ለቁም ነገር አድርሰዋል:: የሁለቱ ባልና ሚስት የግል ሕይወታቸውም ሆነ ለአገር ያበረከቱት የአርበኝነት ተጋድሎ ምሳሌነቱ የጎላ ነው::